ይህ ተግዳሮት በዚሁ ከቀጠለ የምናልመው የዕድገትና የብልፅግና ጉዞን ያደናቅፋል፡፡ በመሆኑም እንደከዚህ ቀደሙ በተገኘው መድረክ ሁሉ የሙስናን አስከፊነት፣የሚያደርሰውን ጉዳት በመደስኮር ብቻ ይህን ነቀርሣ የሆነዉን የመልካም አስተዳደር ችግር ማስወገድ አይቻልም፡፡ አሁን ከመቼውም ጊዜ በላይ የፀረ-ሙስና ትግሉ ከንግግር ባለፈ ተግባራዊ እርምጃን ይሻል፡፡ በመሆኑም በፀረ-ሙስና ትግል ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው የተገለፁ አካላት በሙሉ የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ በአጠቃላይ፤ ቀጣዩ የኢትየጵያ የፀረሙስና ትግል ምዕራፍ ሕዝባዊ መሰረት ያለዉ፤ የባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ ያረጋገጠ፤ መረጃና ዕዉቀት ላይ የተመሰረተ ከንግግር ተሻግሮ በተግባር ለዉጥ ያሳየ ሊሆን ይገባል፡፡ ሙስና እና ብልሹ አሠራር መለየት፤ ማጋለጥ እና ማረም እንዲሁም የሥነምግባርና የሞራል እሴቶች ግንባታ ጎንለጎን ተያይዘዉ ሊሰሩ ይገባል፡፡ ይህን የዕድገት፤ የልማትና የመልካም አስተዳደር ነቀርሳ የሆነዉን ሙስና ከሥር መሰረቱ ለመንቀል ሁሉም እንደየሚናዉ ቁርጠኛ መሆን ይገባል፡፡



**በአዲስ አበባ ኮሙኒኬሽን ቢሮ**

**የህዝብ ሚዲያ ግንኙነትና ይዘት ዘርፍ እና**

**የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስናዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የተዘጋጀ**


*Websites* http://www.cityaddisababa.gov.et/

የአዲስ አበባ ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ
Addis Ababa City Communication

addisababacommunication@gmail.com

https://t.me/AAcommu


# የፀረ-ሙስና ቀን

# "ሙስናን መታገል በተግባር!"



ህዳር 2015 ዓ.ም

ሙስናና ብልሹ አሰራር ልማትን በማዳከም የሀገር ኢኮኖሚ እንዲገታ፣ የሞራልና የሥነምግባር ቀውስ እንዲባባስ፣ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር፣ ህዝብ በመንግስትና በህግ የበላይነት ላይ አመኔታ እንዲያጣ የሚያደረግ አደገኛና ድንበር ዘለል ባህሪ ያለው ዓለማቀፋዊ ወንጀል ነው፡፡

ሙስና ደረጃው ይለያይ እንጂ በሁሉም የዓለማችን ሀገራት የሚገኝና የሁሉም ሀገራት ተግዳሮት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የችግሩ ዋነኛ ተጠቂዎች እንደአፍሪካ ያሉ ታዳጊ ሀገሮች ናቸው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚህ አደገኛ ወንጀል ተጠቂ ነች፡፡ የዓለም ህዝብ ይህን ድንበር የለሽ ዓለምአቀፋዊ ችግር በአግባቡ መከላከል እና መዋጋት ካልቻለ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገትን እንዲሁም ሰላምና መረጋጋትን ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም፡፡በመሆኑም ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ሀገሮች በተናጠል ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ በተጨማሪ በጋራ ለመታገል የሚያስችላቸው ዓለምአቀፍ ኮንቬንሽን እንዲኖር በተባበሩት መንግስታት ድርጅት በኩል ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡በተደረገው የረዥም ጊዜ ጥረትም የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን ተረቆ እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 9-12/2003 በሜክሲኮ “ሜሪዳ” ከተማ ለአባል ሀገራት ለፊርማ ቀርቧል፡፡ የመንግስታቱ ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤም በውሳኔ ቁጥር 58/422 ኮንቬንሽኑ እንዲፀድቅ አድርጓል፡፡ ኮንቬንሽኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአባል ሀገራት ለፊርማ የቀረበበትን ቀን ለማሰብም ዲሴምበር 9 በኢትዮጵያ አቆጣጠር ደግሞ ህዳር 30 ዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን ተብሎ እንዲሰየም ወስኗል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያም የተባበሩት መንግሥታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽንን ከማርቀቅ ጀምሮ እስከ ማፅደቅ በነበረው ሂደት ንቁ ተሳትፎ ስታደርግ መቆየቷ የሚታወስ ሲሆን ከዚያ በኋላም በዓለምአቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ለሚገኘው የፀረ-ሙስና ትግል አጋርነቷን በማሳየት ላይ ትገኛለች፡፡ የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽንን ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 26/2007 በአዋጅ ቁጥር 544/1999 በማፀደቅና የሀገሪቱ የህግ አካል እንዲሆን በማድረግ ረገድም ሀገራችን የራሷን ሚና ተጫውታለች፡፡ ኢትዮጵያ የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ አንድ አካልና የኮንቬንሽኑ ፈራሚና አፅዳቂ እንደመሆኗ ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን ላለፉት 17 ዓመታት ስታከብር ቆይታለች፡፡ ዘንድሮም በዓለምአቀፍ ደረጃ ለ19ኛ በሀገራችን ደግሞ ለ18ኛ ጊዜ የሚከበረውን ዓለምአቀፍ የፀረሙስና ቀን ታከብራለች፡፡በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ18ኛ ጊዜ የሚከበረው ዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን ***"ሙስናን መታገል በተግባር!"*** በሚል መሪ ቃል ይከበራል፡፡ መሪ ቃሉ የተመረጠው የሙስናን ምንነትና የሚያስከትለውን ዘርፈ-ብዙ ጉዳት ከማወቅና ከመረዳት ባሻገር የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶችን ባለመፈፀም፣ በሌሎች ሲፈፀምም አምርሮ በመታገልና በማጋለጥ የተግባር ሰው መሆን ሙስናን ትርጉም ባለው መንገድ ለመታገል ወሳኝ መሆኑን ለማመላከት/ለማስገንዘብ ነው፡፡በሀገራችን እንዲሰፍን የምንፈልገውን ሁሉንአቀፍ እድገትና ብልፅግና ለማረጋገጥ የመልካም አስተዳደር ችግር የሆነውን ሙስናን አምርሮ በተግባር መታገል እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በየደረጃው የሚገኘው አመራር ሙስና በሀገር ላይ የሚያስከትለውን አስከፊ ገፅታ ተረድቶ ተግባራዊ ምላሽ ካልሰጠ የኢትዮጵያን ብልፅግና ማረጋገጥ ከቶውኑ አይቻልም፡፡ በመረዳት በፀረ-ሙስና ትግሉ እያሳየ የሚገኘው ቁርጠኝነት ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ይህም ለፀረ-ሙስና ትግሉ ትልቅ አቅም ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ውጤታማ መሆን የሚችለው በየደረጃው የሚገኘው ሁሉም አመራርና ህብረተሰብ ከቃላት ባለፈ በተግባር ሙስናና ብልሹ አሠራርን መታገል ሲችል ብቻ ነው፡፡ በሀገራችን ሙስናና ብልሹ አሠራር ሥር እየሰደደ ለመምጣቱ የህብረተሰቡ እሮሮና በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች አመላካች ናቸው፡፡